# ከትምህርት የቤት ስራ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ደንቦች -
# የአንደኛ ደረጃ

## I. ሁሉም ትምህርት የቤት ስራ አሰጣጥ ደንቦች

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የቤት ስራ አሰጣጥ ደንቦች ተአማኝ የሆኑ፣ ትርጉም ያላቸው እና አሳታፊ መሆን አለባቸው። ምን ውጤት እና ምን መሰራት እንደሚጠበቅ በዝርዝር በግልፅ የሚያሳዮ በተለየ እያንዳንዱን ነጥብ የሚገለፅ ግልፅ መመሪያዎች ይኖራቸዋል። እነዚህም በትክክል በግልፅ የተቀመጡ አላማዎችና የመገምገሚያ መስፈርቶች ተማሪዎችና ወላጆች ስራውን በሚገባ ያጠናቀቁ ስለመሆናቸው ለማወቅ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መስፈርቶች መሆን አለባቸው። ውጤታማ የሆኑ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የቤት ስራዎች በተጨማሪ፤

- ተማሪዎችን ዝግጁ እንዲሆኑ፣ በዚያ ላይ መሰረት እንዲያደርጉ እና/ወይም በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን በማሳደግ ያግዛል።
- የተማሪዎችን ሃላፊነት፣ የግል ተጠያቂነት እና ተሳትፎ የበለጠ ያጠናክራል።
- የተማሪውን እድሜ እና የእድገት ደረጃ ያገናዘብ ተገቢ መሆን አለበት።
- በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት የትምህርት የንባብ ደረጃ ልዩነት ጭምር ማገናዘብ አለበት።

የኮርስ የቤት ስራ የተለያየ መሆን ይገባዋል እንደ ተማሪዎቹ ፍላጎት የሚለያይ መሆን አለበት እና የሚቻል ከሆነ ልዩነት በተማሪው ሁኔታ፣ የመጀመሪያ ቋንቋ፣ የማጠናከሪያ ድጋፍ እና /ወይም የተግባር አፈፃፀም እና የቤተሰብ ድጋፍ ዝዴ ሲስተም መሰረት ሊለያይ ይችላል።

## II. ከክፍል ውጭ የሚሰጡ ትምህርት የቤት ስራዎች

ከክፍል ውጭ የሚሰጡ ትምህርት የቤት ስራዎች በምርምር ላይ የተመሰረተ ሃሳብ የሚፈለገው የጊዜ መስፈርቶች ማመልከት ይኖርበታል። የሚከተሉት ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ የቤት ስራዎች በእያንዳንዱ የአንደኛ ደረጃ ክፍል የጊዜ ምደባ በተመለከተ የቀረቡ ሃሳቦች ናቸው (በየቀኑ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ስራዎች የሚመደቡ የጊዜ መጠን በሳምንት አራት ምሽቶች ለአንድ መደበኛ ተማሪ)፤

| | ከክፍል ውጭ የሚሰጡ የቤት ስራዎች-<br>በቀን ውስጥ መሰጠት ያለበት ከፍተኛው ደቂቃ | ከክፍል ውጭ የሚሰጡ የንባብ ልምምድ-<br>በየቀኑ ቢያንስ ሊደረስበት የሚገባ ትንሹ የደቂቃዎች ግብ<br>(ለራስ ማንበብ ወይም ከመዋእለ ህፃናት - 2 ክፍል እንዲነበብላቸው።) |
|---|---|---|
| የሕፃናት መዋያ፤ | 0 | 15 |
| 1ኛ ክፍል | 10 | 20 |
| 2ኛ ክፍል | 20 | 20 |
| 3ኛ ክፍል | 30 | 20 |
| 4ኛ ክፍል | 40 | 20 |
| 5ኛ ክፍል | 50 | 20 |

አስተማሪዎች ከክፍል ውጭ የሚሰጡ ትምህርት የቤት ስራዎች መካከል የትኞቹ ነጥብ እንደሚሰጣቸው መለየት አለባቸው። በሁሉም ሁኔታዎች ተማሪዎች ከክፍል ውጭ የሚሰጡ ትምህርት የቤት ስራዎች በተመለከተ አስተያየት ማግኘት አለባቸው። በተከታታይ የተሰጣቸውን የቤት ስራዎች በወቅቱ አለማጠናቀቅ ሁኔታ ከተፈጠረ አስተማሪው ከተማሪው ወላጅ/ አሳዳጊ ጋር መገናኘት ይኖርበታል።

አስገዳጅ የአንደኛ ደረጃ የሚሰጡ ትምህርት የቤት ስራዎች በረዝም የእረፍት ግዚያት ወቅት መስጠት አይኖርበትም ። (ለምሳሌ ፤ ታንክስ ግቪንግ፣ በክረምትና በስፕሪን እረፍት ወቅቶች ወዘተ…) የረዝም ጊዜ ፕሮጀክቶች ስራው ማስረከቢያ ጊዜ ከመድረሱ ቢያንስ ሁለት ሳምንታት በፊት መስጠት አለባቸው ።

| | | |
|---|---|---|
| የፀደቀው፤ | ሜይ 19፣ 2016 | |
| የሕግ ማጣቅሻ፤ | የቨርጂኒያ ህግ 1950 እንደተሻሻለው § 22.1-7822.1-78 | |
| የቃላት መፍቻ፤ | IFA | ምዘና እና ግምገማ |
| | IFA-R | ምዘና እና ግምገማ |
| | IKD | የትምህርት የቤት ስራ አሰጣጥ- የአንደኛ ደረጃ |
| | IKA | በትምህርት አሰጣጥ የወላጆች ተሳትፎ |